
ሣዕየ ሕይወት

ዲጂታል መጽሔት ልዩ አትም ቅጽ 2 ቁጥር 3 ጎንደር 2019 ዓ.ም.



ዋና አዘጋጅ

- በትምህርት እና ሥልጠና ክፍል
  መጽሐፍ እና መጽሔት ዝግጅት ንዑስ ክፍል

አዘጋጅ

- ልድያ አቦወርቅ
- ሜላት ክብረት
- ሜሮን ተስፋዬ
- ዕፁብ ታከለ
- ቅድስት ግዛቸው
- ቅድስት ፀጋዬ

አርታኢ

- ጉባኤ አርትዖት ክፍል

ግራፊክስ ዲዛይን

- ረድኤት ሰብስቤ

ኅዳር 2019 ዓ.ም.

ማውጫ

03 ሥጋዬ መቅደስ...ነፍሴስ ወዴት ናት?

04 በሰማይ የድል ዝማሬ፣ በምድር የተስፋ ብርሃን

05 አፈ ወርቅ . . .

07 እስከ ማዕዜኑ

10 ይህ ልቤ . . .

ሥጋዬ መቅደስ . . . ነፍሴስ ወዴት ናት?

በዲ/ን ዮሐንስ በላይ

03

የሰንበት ማለዳ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ በምእመናን ተሞልታለች። የቅዳሴው ማኅሌት፣ የካህናቱ ዜማ፣ የዲያቆናቱ ዝማሬ ከዕጣኑ ጢስ ጋር ተዋሕዶ ወደ ሰማይ ያርጋል። መላእክት ከአኛ ጋር ሆነው የሚያመሰግኑበት፣ ምድር ሰማይን የምትመስልበት ድንቅ ሰዓት ነው። እኔም ከቅዳሴው ተካፋዮች አንዱ ሆኜ ጥግ ጋር ቆሜያለሁ። ካህኑ "እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን" ሲሉ፣ "ከመንፈስህ ጋር" እያልኩ እመልሳለው። በውስጤ ግን የተለየ ስሜት ይብላላ ነበር። 'እንዴት ደስ ይላል . . . ዛሬ አምልጬ አልቀረሁም፤ ዓለም በአንቅልፍና በኃጢአት ሲንከባለል እኔ ግን መቅደሱ ውስጥ ነኝ' የሚል ስውር የትዕቢት መንፈስ ፀሞግተኖል። ከንፈሬ ጸሎት ይደግማል፤ ዓይኖቼ ግን መቅበዝበዝ ጀመሩ። አጠገቤ ያሉትን እያማተርኩ አንዳንዱን ማየት ጀመርኩ። 'ይህች ደግሞ አትከናነብም እንዴ? ያኛው ደግሞ ቅዳሴ ላይ ስልክ ያያል፤ አገሌ ደግሞ ዛሬም አልመጣም . . .' እያልኩ ቤተ መቅደሱን የጸሎት ቤት መሆኑን ዘንግቼው፣ የራሴን የፍርድ ዙፋን ዘርግቼ በወንድሞቼ ላይ መፍረድ ጀመርኩ።

ራሴን ጻድቅ፣ ሌላውን ኃጢአተኛ አድርጌ ሾምኩ። የለበስኩት ነጭ ነጠላ፣ የውስጤን ጥቁረት የሸፈነልኝ መሰለኝ። ድንገት ግን የዲያቆኑ ድምፅ ቤተ መቅደሱን ሞላው . . . " . . . ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ!" ብሎ አወጀ። እኔም እንደ ሁሉም ፊቴን ወደ መቅደሱ አዞርኩ። በዚህ ቅጽበት ግን ሕሊናዬ እንደ መብረቅ የሚያንቀጠቀጥ ከባድ ጥያቄ ወረወረብኝ፦ 'አንተ ግብዝ . . . ፊትህ ወደ ምሥራቅ ዞሯል፤ ልብህ ግን ወዴት ነው ያለው? ሥጋህ አዚህ መቅደስ ቆሟል፤ ነፍስህ ግን በየትኛው የሐሜት ገበያ እየተንከራተተች ነው?' ልክ ባለፈው ጊዜ መርሐ ግብር ላይ "ማንን ትሾኑ ነበር?" ብለን፣ በክርስቶስ ዘመን ብንሆን ኖሮ ከማን ወገን እንደምንሆን ራሳችንን እንደጠየቅነው ሁሉ፣ ዛሬም በቤቱ ሆኜ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ። ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዓለምን ሲያድን፣ እኔ አዚያ ብገኝ ኖሮ በእርግጥ ከማን ጎን እቆም ነበር? ዮሐንስን ሆኜ ከሥሩ አገኝ ነበር ወይስ እንደ አዩሁድ 'ከመስቀል ውረድ' እያልኩ እዘብትበት ነበር? ዛሬ በቤቱ ቆሜ፣ በደሙ በተገዛው ወንድሜ ላይ የምፈርድ፣ በትዕቢት የምመጻደቅ እኔ፣ ያኔ ብኖር ኖሮ ጌታን የሰቀሉት እጆች የኔም እጆች አዩሆኑም ነበር? አአምሮዬ መቆሚያ አጣ።



ይሁዳ ከጌታ ጋር ሦስት ዓመት ሙሉ አብሮ በልቷል፣ ጠጥቷል፣ ተአምራቱን አይቷል። ሥጋው ከጌታ ጋር ነበረ፣ ልቡ ግን ከሠላሳው ብር ጋር ነበር። እኔስ? በሥጋዬ ቤተ ክርስቲያን ቆሚያለሁ፤ ልቤ ግን በዓለም ምኞት፣ በክፋት፣ በወንድሜ ላይ በመፍረድ ይዞራል። ከይሁዳ በምን ተለየሁ? ጴጥሮስ በድንጋጤ ሦስት ጊዜ ካደ፣ እኔ ግን እያወቅኩ፣ ቃሉን እየሰማሁ በዕለት ምግባሬ ስንት ጊዜ እክደዋለሁ? ፈሪሳዊው 'እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንኩ አመሰግንሃለሁ' ብሎ ጸልዮ፣ ጸጋውን አጥቶ፣ ባዶውን እንደተመለሰ . . . እኔም 'እንደነከሌ ስላልሆንኩ፣ ጠዋት ተነስቼ መቅደስ ስለመጣሁ . . .' እያልኩ ቤተ መቅደሱን የኩነኔ አደባባይ አደረግሁት። እግዚአብሔር የሚፈልገው የተቀጠቀጠና የተዋረደ ልብ ሆኖ ሳለ፣ እኔ ግን በሌሎች ድካም ላይ የራሴን የውሸት ጽድቅ እየገነባሁ እንደሆነ ታወቀኝ።

ካህኑ "ቅዱስ የሆነው ለቅዱሳን ይሰጣል ሲሉ፣ ይበልጥ ደነገጥኩ። የቱ ቅድስናዬ? ወንድሙን በልቡ እየጠላ፣ የሰውን ኃጢአት እየቆጠረ የሚውል አአምሮ ይዞ፣ እንዴት ይህንን የሰማይ ድምፅ መስማት ይቻላል? 'እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ' ስንል፣ ከንፈሬ እንጂ ልቤ አብሮ አልጮኸም። ቅዳሴው አብቅቶ ካህኑ "በሰላም ግቡ" ሲሉ፣ ወደ ቤቴ መሄዴን ትቼ ወደ ራሴ መመለስ፣ ወደ ልቤ ማልቀስ ፈለግሁ። አሁን ወንድሞቼ እና እኅቶቼ፣ እናንተንም ልጠይቃችሁ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነን ፤ ሥጋችን አዚህ ነው። ልባችን ግን የት ነው? ስንቶቻችን ነን በቤቱ ቆመን ከቤቱ የራቅን? ስንቶቻችን ነን ቃሉን እየሰማን በሐሜት ጌታን ዳግም የምንሰቅለው? በመስቀል ፊት ቆመን ፍቅርን ከመማር ይልቅ፣ ጥላቻን የምናቀፈው ስንቶቻችን ነን? እስቲ ዛሬ ራሳችንን እንዋሽ፤ ቆም ብለንም እናስብ። ዛሬ ማንን እየሆንን ነው? ሥጋችን አዚህ ነው . . . ነፍሳችንስ?

"በሰማይ የደል ዝማሬ፣ በምድር የተስፋ ብርሃን!"

04

በሚካኤሌ ተክሌ



በጎዳር ወር የሚካኤል በዓል ሲደርስ፣ የበዓሉ ደወል ብቻ አዩደለም የሚሰማው፤ የእምነት ልብ በምስጋና ዩነቃል፣ የተስፋ ምንጭም በውስጡ ዩፈልቃል። የቅዱስ ሚካኤል ስም በአንደበታችን ሲጠራ፣ ሐሳባችን ወደ ሰማያዊው ክብር ዩመራል፤ ልባችንም ከዓለም ጫጫታ ተለዩቶ ወደ መንፈሳዊው ሰላም ዩጓዛል። ጎዳር ሚካኤል በዓል ብቻ ሳዩሆን፣ የእምነት መታደስ፣ የተስፋ መነቃቃትና የመንፈስ መጽናኛ የሚሆን ታላቅ መታሰቢያ ነው።

ቅዱስ ሚካኤል! ስሙ በራሱ ስብከት ነው። "ማን እንደ እግዚአብሔር ነው?" የሚለው የስሙ ትርጉም ለፍጥረታት ሁሉ የሚያውጅ አንድ የማዩለወጥ እውነት አለው፤ ከፈጣሪ የሚበልጥ የለም፣ ከሥልጣኑ የሚበረታ የለም፣ ከጥበቡም የሚበልጥ የለም። ስለዚህ የሚካኤል ስም ሲነሣ ልባችን ወደ ፈጣሪው ዩመለሰል፤ የሰው ኃዩል ውስን ቢሆንም የእግዚአብሔር ሥልጣን ወሰን እንደሌለው እናስባለን። የሰው ጥበብ ቢያጥርም የፈጣሪ ጥበብ እንደማዩጎድል እንማራለን።

በዮሐንስ ራእዩ መጽሐፍ፣ "በሰማዩም ጦርነት ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱም ከዘንዶው ጋር ተዋጉ" ራእ 12÷7 ተብሎ ተጽፏል። ዩህ ቃል የክፋትና የጽድቅ ተቃርኖን፣ የሰዩጣንን ዓመፅና የእግዚአብሔርን የማዩሸነፍ ሥልጣን ያሳያል። ቅዱስ ሚካኤልም በዚህ የተጠቀሰው በሰማያዊው ጦርነት የተሳተፈ ሊቀ መልአክ ሆኖ ነው።

ስለ መላእክት አገልግሎት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፣ "ሁሉም ለማገልገል የሚላኩ መናፍስት አዩደሉምን?" ዕብ 1÷14 በማለት ዩጠዩቃል። ዩህም መላእክት በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚያገለግሉ መንፈሳዊ ፍጥረታት መሆናቸውን ያስረዳል። ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን ስታከብር አምልኮን ለእነርሱ አታቀርብም፤ አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ቅዱሳንን ማክበር ግን እግዚአብሔር በእነርሱ ያደረገውን ጸጋና ቅድስና ማሰብ ነው።

የሰው ሕዩወት በተለያዩ ፈተናዎች የተሞላ ነው። እንዳንዴ በመከራ፣ በጭንቀት፣ በቤተሰብ ችግርና በውስጣዊ ትግል እንፈተናለን። በእነዚህ ጊዜያት አምነታችንን ማጽናት፣ በጸሎት መትጋትና ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ዩገባል። ሐዋርያውም "እምነትን የሚያጸናውን የእምነት ጦር ያዙ" ኤፌ 6÷17 በማለት በመንፈሳዊ ትግል መጽናት እንዳለብን ያስተምረናል።

ስለዚህ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል ስናከብር ከኃጢአት፣ ከትዕቢት፣ ከቅናትና ከጥላቻ ጋር እንታገል፤ በጸሎት እንትጋ፣ በጽድቅ እንመላለስ፣ ለተቸገሩት እንርዳ፣ ከክርስቶስ ማዕድ እንሳተፍ፣ የተጣሉንም እንታረቅ። የበዓሉ መንፈሳዊ ፍሬ በሕዩወታችን የሚገለጠው በዚህ መንገድ ነው።

ወዳጆቼ ጎዳር ሚካኤል የበዓል ልብስ የምንለብስበት፣ በመቅደስ የምንሰበሰብበትና በዝማሬ የምናመሰግንበት ቀን ብቻ አዩደለም። አምነታችንን የምንመረምርበት፣ ሕዩወታችንን የምናስተካክልበትና ከክፋ ሥራ የምንመለስበት የመንፈሳዊ እድሳት ቀንም ነው። ቅዱስ ሚካኤል ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚቆም ሊቀ መልአክ መሆኑን ስናስብ፣ እናም በዓለም ፈተና ውስጥ በእምነት እንድንጸና፣ በጽድቅ እንድንመላለስና በፍቅር እንድንኖር እንነሣሣለን።

እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቤን ጠብቅ ብሎ የሾመው ታላቁ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል፣ ሁልጊዜም ለፈጣሪው ሕዝብ የሚቆም የድል አርማ ነው። ቅዱስ ሚካኤል ሆዩ "የዲያቢሎስን አሰራር በጣጥሰህ ትጥልልን ዘንድ አኛ ልጆችን እንለምንሃለን።"

አፈ ወርቅ . . . 05

"ሰላም ለፍልሠተ ሥጋከ፤ ፍለጋው በሚበራ መብራት በተደረገለት ልዩ በኾነ በመስቀል በዓል ቀን ለተደረገው የሥጋህ ፍልሰት ሰላምታ ፀገባል። ሐዲስ ኪዳንን የምትተረጉም የጳጳሳት አለቃ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ሆዩ ተአምርን የሚሠራ አካልህ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ሮም ቢፈልስም በታላቅ ምስጋና ወደ መንበሩ ወደ ቊስጥንጥንያ ተመለሰ ።" መልክዐ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ነገረ ቅዱሰንን በምንማማርበት በዋኖቻችን ዓምዳችን ለዚህ ወር በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የብሩህ አዕምሮ፣ የመንፈሳዊ ብርሃን፣ የእውነት ምስክርና የንጽሕና ምሰሌ የሆነውን ታላቁን ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን በማዘከር ከሕፀወቱ አናተርፋለን። መልካም ንባብ።

በአንጾኪያ ምድር በ347 ዓ.ም. የተወለደው የታላቁ ሊቅ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አባት ሲፋኒዶስ (ሴኩንዱስ) የታወቀ አገረ ገዥ የነበረ ቢሆንም በለጋ ዕድሜው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ እናቱ አንቱዛ (አትናስያ) በ20 ዓመቷ በመበለትነት አሳድጋዋለች። ያሳደገችውም እጅግ መልካም በሆነ በጥልቅ ክርስቲያናዊ ምግባርና ዕውቀት የነበረ ሲሆን በልጅነቱም የፍልስፍና ትምህርትን ከአንድሮጋቶስ፣ የንግግር ክህሎትን ደግሞ ከሊባንዮስ ተምሯል።



በትምህርት ቤት ቆይታው ከቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ ጋር ያፈራው መልካም ወዳጅነት ለቀጣዩ የመንፈሳዊ ሕፀወቱ ትልቅ መሠረት ሆኖታል። በፍርድ ቤት በጥብቅና ሙያ ያገለገለ ቢሆንም በወቅቱ የታዘባቸው ዓለማዊ ብልሹ አሠራሮችና የጓደኛው የባስልዮስ ተጽዕኖ ሥራውን በፈቃዱ አንዲለቅ አድርገውታል። በኋላም ምንም እንኳን ወደ ገዳም መሄድ ቢፈልግም እናቱ ጋር መቆየት ስለነበረበት እርሷን እያገለገለ በእናቱ ቤት የምናኔን ሕፀወት መለማመድ ጀመረ። የሦስት ዓመት የንዑሰ ክርስቲያንነት ትምህርት ተምሮ ካጠናቀቀ በኋላም በ23 ዓመቱ በአባ መላጥዮስ እጅ ተጠመቀ። የፍጹም ትጋቱ መግለጫ ፀሆን ዘንድም የአናጉንስጢስ (አንባቢነት) መዓርግ ተሰጠው።

ከእናቱ ዕረፍት በኋላ የወረሰውን ሀብት ለድሆች መጽውቶ ከአንጾኪያ በስተደቡብ በሚገኝ ገዳም ውስጥ የምንኩስና ሕፀወቱን ጀመረ። በገዳሙ አራት ዓመት፣ በዋሻ ውስጥ ደግሞ ለሁለት ዓመት በጾምና በጸሎት ተወሰነ። በዚያም በራእፀ አባ ሲሲኮስ ለተባሉ አባት ቅዱስ ጴጥሮስ ቀልፋ፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ ደግሞ ወንጌልን ለቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሲሰጡት ታፀቷል። ሊቁም በ381 ዓ.ም. በአባ መላጥዮስ እጅ ዲቁናን በ386 ዓ.ም. ደግሞ በአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ፍላቭያኖስ እጅ ቅስናን ተቀብሏል። በቅስና ዘመኑም ለ12 ዓመታት ያህል ወንጌልን በድፍረት ሰብኳል። ንጉሡ ቴዎዶስዮስ በሕዝቡ ላፀ ቀረጥ በማብዛቱ ሐውልቱ ሲፈርስ "በእንተ ሐውልታት" በሚል ርእስ ያስተማረው ትምህርትና አርዮሳውያንን በመቃወም ያደረገው ተጋድሎ ለትጋቱ ምስክርነት በስፋት የሚጠቀሱ ናቸው።

በ397 ዓ.ም. የቊስጥንጥንያው ፓትርያርክ ኒክታሪዮስ በማረፉ፣ ቅዱስ ዮሐንስ በየካቲት 26 ቀን 398 ዓ.ም. ያለ ፈቃዱ ከትውልድ ሀገሩ ተወስዶ የቊስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ። በጵጵስና ዘመኑ የሊቃነ ጳጳሳትን ልብስ ትቶ ያረጀ ፀምር ፀለብስ፤ ሥጋዊ ፍላጎቱን ለማሸነፍም በመሣል እጁ የሚወሰን የገብስ ጥሬ ብቻ ፀመገብ ነበር።

ንግሥት አውዶክስያ ሥልጣኗን ተጠቅማ የአንዲትን መበለት መሬት በነጠቀች ጊዜም ድሃዪቱን እንድትመልስላት ደጋግሞ አሳሰባት። ዩሁን እንጂ ንግሥቲቱ አምቢ ብላ ነበርና ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብታ ሥጋውን ደሙን እንዳትቀበል ስላወገዛት በበቀል በጠላቶቹ አማካኝነት በስደት ወደ ደሴተ አጥራክያ እንዲጋዝ አደረገችው። ንጉሥ አኖሬዎስ ባደረገው ግፊት ተመልሶ ቢመጣም፣ ንግሥቲቱ እንደገና በስደት እንዲያዝ አደረገች። በመንገድ፣ በአስራት በታላቅ ድካም ሰቢያም አጥራክያ እንደደረሰ ግንቦት 12 ቀን 407 ዓ.ም. በሰላም ዐረፈ። ኋላ ላዩ የሮሙ ንጉሥ አኖሬዎስ እና ሊቀ ጳጳሱ ዮናክንድዮስ ስለ አርሱ ንግሥቲቱን ሲያወግዟት፣ በከባድ ደዌ በመያዟ ወደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ መቃብር ጋር ሄዳ በእንባ ተማጽና ከደዌዋ ድናለች።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ መአር፣ አፈ ሶከር፣ አፈ በረከት ፣ ልሣነ ወርቅ፣ አፈ ወርቅ ፣ ዳንኤል ሐዲስና በሌሎችም ስሞች ይታወቃል። የአንደበቱን ጣዕም የማይጠገብ፣ ፍትህ ሲጓደል ስልጣንን ሳይፈራ ከተጨቆኑት ጎን በመቆም እውነትን ለመናገርና ለተግሳጽ የማይዘገይ ፣ በትምህርቱ እጅግ ብዙ ሰዎችን የመለሰ ፣ ዓለማዊ ከንቱነትን ንቆ ሙሉ ሕይወቱን ለአገልግሎት በመስጠት ክርስትናን በመኖር ሕይወቱ ብርሃን የሆነ ሊቅ፣ ቅዱስ አባት ነው።

አምላከ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቃልኪዳን ይማረን!



ምንጭ፦

- መጽሐፈ ስንክሳር
- መጽሐፈ ምሥጢር
- ድርሰነ ሠለስቱ ሊቃውንት
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሕይወቱና ትምህርቱ

እስከ ማዕዜኑ 07

ሀገር ታምሰለች መቼ፣ በምን ሰዓት እና ሁኔታ እዚህ እንደተገኘን አዬገባኝም አዬደለም ጦርነት መሳል ተዋጊ ሆኜ ራሴን ላገኘው ቀርቶ ዬህንን የተመለከተ ርዕሰ ጉዳዬን መስማት እንኳን የሚረብሸኝ ሰው ነበርኩ። አዬገርምም ነበርኩ እንደዚህ በሕዬወት አዙሪት በነገሮች ፍሰት ወስጥ በቀላሉ የምትጠቀስ ቃል መሆኗ አዬገርምም አእምሯችን መሆንን እና ሐሳቡን በቅስፈት ለውጦ ነበርን ሲተካ በሕዬወት ነበርን ማለት እንከማትችልባት ሁነት ድረስ መስመራችን ሁሉ እንዲሁ ነበርን በሚል ቃል የተሞላ ነው። ኤርምያስን የማውቀው ጦር ሜዳ ነው የጭንቅ ቀን ጓድ እንደ እድል ሆኖ ከሥልጠና እስከ ተመደብንባቸው ቦታዎች ድረስ አልተለያየንም አንዳንዴ እግዚአብሔር በዚህ መሳል ለመፍትሔ ያስቀመጠልኝ የእርሱ መኖር እንዳልረሳ የሚያስታውስበት ፍጥረቱ ዬመስለኛል። ኤርምያስ ቆፍጣና ነው ሲፈራ አላውቀውም "ሆኖ ከመጣ በኋላ የምን ወደኋላ" ዬሳል ሁሌም የጦር ሰፈር ወሬ እንዲህ የሚተርኩት ቃላት በቀላሉ የሚሰኩለት አዬደለም። ሰው ቅጠል ሆኖ ሲረግፍ ፤ አለ እና የለም የሰከንድ ጉዳዬ ሲሆን እያየሁ መጥቻለሁ።

ያ ሁሌም ዜማ ከአፋ የማያጣው ጦርሜዳን ቤተ መቅደስ ያደረገው ኤርምያስ አቤት የድምጹ ውበት እንዳንዴ እረፍት ያገኘንበት ቦታ ላዬ ያለሚቋረጥ ዓዬኑን ጨፍኖ የሳላቃቸውን የግእዝ ቃላት ከተሰተረ ውብ ዜማ ጋር ያወርደዋል ያ ተስፋ ዬሰጠኛል ፤ ያ ነገን ያስናፍቀኛል ደግሞ ዝም ዬልና "አዬዞህ ወንድሜ ከዚህ እንወጣለን ከዛ በመቅደሱ ነጠላችንን ለብሰን ውዳሴዋን እናደርሳለን ናዛዚትነ እመ ብዙኃን እንላታለን" ዬለኛል፤ እንዲሁ ነው የኖርነው።

እስከዛች አበባ ድረስ በረኃ መሳል ከጠላቶቻችን ሸሽተን በሌሊት ምድረ በዳውን እየተጓዝን ኤርምያስ ለብቻዋ ድንጋዬ ስር የበቀለች እንዲች ጽጌሬዳ አየ እናቱን እንዳየ ሕጻን ሮጦ ቀጠፋት በርግጥ በረኃ ውስጥ መገኘቷ ተአምር ቢሆንም እርሱ ፊት ላዬ ከነበረው ደስታ የሚበልጥ ግን አልነበረም "እኔ የምልህ" አለኝ ዓዬኖቼን ተከዬ የሚለኝን ለመስማት ተዘጋጀው "ወረ ጥቅምት ነው አዬደል" ድምጹን ለስለስ አድርጎ አዎ የመጨረሻዋ ቅዳሜ አልኩ "ዘመነ ጽጌ ባለ አበባዋ ወር" አለኝ ምንድነው የሚለፈልፈው ዬህ ሰው ዬለኛል ልቤ "በዚህ ሰዓት በመቅደሱ የአበባ እቅፍ ዬዜ ጽናጽሌን እያሰማሁ አክሊለ ጽጌ ማርያም ቀጸላ መንግሥቱ ለጊዮርጊስ እያልኩ ነበር በዚህ ሰዓት ከበሮዬን ዬዜ እስከማዕዜኑ እግዝአትየ እያልኳት ነበር"

ዓዬኑን ወደላዬ ሰቀለ ለመጀመሪያ ጊዜ የኤርምያስ ዓዬኖች እንባ አቀረሩ እስከማዕዜኑ ድንግል የዚህች ሀገር መከራ፤ እስከመቼ እመቤቴ የአኖ አዚህ መቆየት፤ እስከማዕዜኑ እመአምላክ መቅደስሽን መናፈቄ፤ መልሺኝ አዛኝቱ ካንቺ ጋር መልሺኝ በቃኝ አዛኝቱ" አነዚህን ቃላት በሲቃ አወረዳቸው እንባው ጉንጮቹን ሞላቸው ዝም ብዬ አየሁት እንዲሁ ዝም ብዬ . . . በዚህ መሳል ግን ጠላት ደረሰ ተኩስ ተጀመረ መውጫ እንዳዬናረን ሆነን ተከበብን እያየሁ ዙሪያዬ በሬሳ ተሞላ፤ እያየሁ ኤርምያስ ግራ ደረቱ ተመታ እና ከአበባዋ ጋር ወደቀ ማዘር ያልቻለውን ፊቱን ሳዬመልስ በህማም ድምጽ እጁን ሰንዝሮ ዬህንን ለማርያም ስጥልኝ አለኝ ያቺን የበረኃ አበባ ለሚወዳት ማርያም ላከኝ ተቀብዬው ሌሎች ጓዶች ጋር ምሽግ ፍለጋ ሮጥን። እንደለመናት በቃቹ የምትለን መስሎኝ ነበር እንደናፈቀው ለመቅደሱ የምታበቃው መስሎኝ ነበር።

አዬ ነበር የማዬወጡት የለም በልብም በአካልም ቁስል ተጎድተን ነገር ሁሉ አለፈ ቀን ተቀየረ ቀን ተለወጠ ያም ጦርነት ነበር ሆነ እናም እኔ የሰጠኝን አበባ ከጦርነት ማስመለጥ ባልችልም ዓመት ተቆጥሮ ለደረስኩባት የጽጌ ወር እቅፍ አበባ ዬዜ የኤርምያስን ምኞት ልፈጽም በመቅደሱ ተገኘሁ።



የሚሉት አልገባኝም ግን ኤርምያስ እንደሚለው ነው እንዴ አበባዬን እንዴ እነሱን እያየሁ ሌሊቱን አጋመስኩት ድካምን ሰላውቃት ኤርምያስ ለመጨረሻ ጊዜ ያዜማት አክሊለ ጽጌ የምትል ዜማ ሰማሁ ቀስ እያለ ሞቀ የመጨረሻውን ዝማሬ ግን ያንን ድንቅ ባለ ዜማ ከከበሮ እና ከተመስጦ ጋር አሳየችኝ ኤርምያስን እየሁት አልሞተም የተማጸናት ድንግል በአርግጥ የናፈቀውን መቅደስ አሳየችው ተስፈንጥሬ አጠገቡ መሆን ፈለኩ ግን የሚሆን አልነበረም ብቻ የቀሩት ሰዓታት የዓመት ያህል ረዘሙብኝ ነገር ግን አለቀ ተሸሎክልኬ ከኋላው ቆምኩ ጠምጥሚል ነጭ ካባ ደርቧል ኤርምያስ እንደዚህ በጣም ያምራል በእጅቼ ከኋላው ነካሁት በቅጽበት ዞረ ተያየን ለረዘመ ሰንከጶች ተያየን በበረኃ በደም ርሰን እንደተያየነው በዚህ በከበረ ቦታ በነጭ ልብስ ተያየን እናም አርሱ በቃኝ እንዳለሁ በበረኛ አበባ ያበረከተላት አመብርሃን አላሳፈረችውም የልቡ ደስታ መቅደሱን መለሰችለት ዩኸው ዘመን ተቀየረ ዘመን ተለወጠ ዛሬም አብረን ማኅሌቷን በእንባ እንቆማለን።

በሜላት ክብረት

ዩህ ልቤ . . .

09

ሌት ተቀን ሲጨነቅ ያድራል ባልሆነው ባልሰመረለት
በራሱ ማድረግን ዩሻል አዩትልም እርሱ ያውቃል
ማለት።
እርጋታ አዩሆንልኝም ታውቃለህ እንደምቸኩል
መታገስ አልችልበትም መራመድ ከእንተ ጋር እኩል።
አዩተሳል ትዕቢት ሲያልፍ በልቤ ቀዳዳ በኩል።
(አዩተሳል መተማመኔን
እንተን ሳዩሆን እኔን!)
እንኳንም ትናንት አልሆነ!
እንኳንም በጊዜህ ሆነ!
አብዝቼ ምን ብጠይቅም
መሸከም እንዳያጎብጥ ያሻዋል
ለፀጋም አቅም።
ለምኜህ ስላልተሰጣ ምን ንጥቂያ እንኳ ቢመስል
ባጣሁት በቀማኸኝ ነው ያዳንከው የልቤን ቁስል።
(መርምሬ ያልደረስኩበት ምክንያትህ ተገለጠልኝ
'አሁን' ስል እንዳትሰጠኝ ብትጠፋስ ብለህ
አዘነህልኝ።)
ባንተ ላይ እንደሆነ አወኩ እምነቴን ተስፋዬን መጣል
ከራሴ ለእኔ ቅርብ ነህ ፈቃድህ ከሐሳቤ ዩበልጣል!
አበቃ ያልኩትም ሁሉ ከልካዩም እንቢ ያለው እንባ
በደስታ ተተክቶ አየሁ አላውቅም የት እንደገባ።
(እንዲሁ ያልፋል በዋዛ
የልብም ጎዘን ዩረሳል
በጊዜህ የሆነው ውብ ነው ትናንትን
በአጥፍ ዩክሳል።)
መሰሰት የለም ከቤትህ አያልቅም ከእጅህ ስትሰጥም
አዩቻለሁ ተአምርህን ምስጋናን አላቋርጥም።
ባቃተኝ በድካሜ ላዩ አ ማ ኑ ኤ ል ሥራህ ገነነ
ትናንትን ያስጨነከኝም ዛሬ ላዩ ለ መ ል ካ ም ሆ ነ።

በሰላም ጥበቡ



ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ዘመነ ሉቃስ
፭፻፲፱ ዓ.ም